# የሰርጎ ገቦችመልክና አሰራር
# (ከትላንት እስከ ቅንጅት ያለውን በመቃኘት)

**ቤልጂግ አሊ**

ወያኔ ኢሕአዴግ በተባለው የሀገራችን ጠላት ላይ በጋራ ተነሳስተው ሲታገሉ የነበሩት ዛሬ እርስ በርስ እየተናከሱና በአደባባይ ገበናቸውን አስጥተው ለመለስ ዜናዊ መሳለቂያ መሆናቸውን ስናይ ቅንጅት የተበላው ድርጅት በሰርጎ ገቦች እየታመሰ መሆኑን መረዳትና ማወቅ እንችላለን።በሞስኮና ኪዬቭ ከቀስምኩት ትምህርትና ለተወሰነ ጊዜም የወያኔን አሰራር በግሌም በመከታተሌ የምፅፈው በግምትና በይሆናል ሳይሆን በእውቀትና ልምድ ላይ በተመካ ሀቅነት ደረጃ ነው።

1. ሰርጎ ገብ ማነው? በጥቅሉ ሲገለፅ ሰርጎ ገብ የአንድን ድርጅት ወይም መንግስት ግብ ለማድረስ በሌላ ድርጅት ውስጥ ተመሳስሎና ተሸፍኖ የሚገባና የሚሰራ ነው/ናት።

2. የሰርጎ ገብ ተልዕኮ የሚወሰነው ሰርጎ ገቡን በሚያሰማራው አካል ወይም ድርጅት ወይም መንግስት ነው። ሰርጎ ገቡ ዜና--መረጃን ለመሰብሰብ ብቻ ሊላክ ይችላል። ወይም በገባበት ድርጅት እርከን ከፍ ብሎ አመራሩ ውስጥ ለመግባት ተልዕኮ ሊሰጠው ይችላል። ወይም ከተነሳንበት ርዕስ ትኩረት ለማየት ደግሞ ሰርጎ ገቡ በድርጅቱ ውስጥ ብጥብጥና ክፍፍልን የማባባስ አፍራሽ ተልዕኮ ሊሰጠው ይችላል። በተደጋጋሚ እሱ እሷ ላለማለት ሰርጎ ገቡ ብልም ሰርጎ ገብ ወንድ ብቻ ነው ብሎ መደምደሙ ትልቅ ስህተት ይሆናል። እንዲያውም በወንዶች በሚካሄዱ ድርጅቶች ወይም መንግስት ሴቶችን የመናቅ ወይም በዝቅ መገመቱ የተለመደ በመሆኑ ሴቶች ከፍተኛ የሰርጎ ገብ ሚና ይጫወታሉ። ከባዕድ ተመክሮ ከተነሳን ለምሳሌ እስራዔል በሴቶች ተጠቅማ የምታካሂደውን መመርምሩ ይጠቅማል። ወደ በኋላ ደግሞ ሰርጎ ገቦችን እንዴት ማሸተት እንደሚቻል ለማየት እንሞክራለን።

3. ካለፈው ተመክሮ ስንቃኝ በጊዜው የነበረው መንግስት ሆነ ተቀናቃኞቹ በየፊናቸው በሰፊው በሰርጎ ገቦች ተጠቅመዋል። የኤርትራ ግንባሮች በተለይም ሻዕቢያ በሴቶች በመጠቀምና ኋላም በገንዘብ አቅም በርካታ ሰርጎ ገቦችን አሰማርቶ ጉዳት አድርሷል። በሰርጎ ገብ በመጠቀም ብዙ ተመክሮ ያለውና አሁንም በዚህ መስክ ስለነበረው እንቅስቃሴ ብዙም የማይለው ኢሕአፓ ነው። ኮሎኔል መንግስቱን ለመግደል ሆነ ለብዙ የመረጃ ስራዎች በደህንነት ውስጥ ባሰማራቸው አባላቱ ተጠቅሟል። ለነገሩ የደርግ አባል ሻለቃ ሞገስና ሌሎችም መኮንኖች አባሎቻቸው ነበሩ። ኢሕአፓ መኢሶንንም ሰደድንም ሰርጎ መግባቱ ደግሞ በደርግም የታወቀ ጉዳይ ነው። ደርግ በበኩሉም በኤርትራ ግንባሮች ውስጥ ሰርጎ ገቦች ነበሩት። የኢሕአፓ መዋቅርና የአመላመል ህግ ለሰርጎ ገብ ስራ ቢከብድም በዚህ ድርጅት ላይም ሆነ በወያኔ ላይ ደርግ የሰርጎ ገብ ማሰማራት ኦፐሬሽኖች እንደነበሩት አውቃለሁ። ከድርጅቶች አንፃር ለሰርጎ ገብ ስራ ቀላል የነበረው ኦነግ መሆኑንም በጊዜው ሲነገር ሰምቻለሁ። ኢሕአፓና ወያኔ እርስ በርሳቸው ሰርጎ ገብን ይላላኩ እንደነበር ቢወራም ዝርዝሩ የሚታወቅ አይደለም። ሁለቱም ግን ሌሎች ተቀናቃኞችን መስረጋቸው ይነገራል። ወያኔ ለምሳሌ በኢዲኅ በመስረግ የኢዲኅ ተቆርቋሪ መስሎ ኢዲኅና ኢሕአፓን ለማጋጨት መሞከሩ ተዘግቧል። ወያኔ ሁሉን ድርጅቶችና ደርግን በስርጎ ገብ ሞልቼ ነበር የሚለው ከሀቅ የራቀ ጉራ መሆኑ ሲነገር ወያኔም ሻዕቢያም ግን ከአሜሪካው የስለላ መዋቅር ብዙ መረጃ መለገሳቸው የሚካድ አይደለም።

4. ለሰርጎ ገብነትየሚደረግ ዝግጅት ለዚህ ስራ የሚታጩ ግለሰቦች በተለይም አደገኛ ሊሆን በሚችል ሁኔታ ለስራው ብቃት ያላቸው መሆኑ በሚገባ በቅድሚያ ይመረመራል። በእርግጥ የሰርጎ ገቦች ዓይነትና ሚና የተለያየ ነው። ዝግ በሆኑና በሰላይ ላይ ከፍተኛ እርምጃ በሚወስዱ ውስጥ የሚሰርግ ህይወቱን ለሞት አደጋ ሰጥቶ ነው። በዛሬው ሁኔታ ግን ክፍት ወይም ህጋዊ በሆኑት ድርጅቶች ሰርጎ መግባት ብዙ የሚያስፈራ ስላልሆነ ከሰርጎ ገቡ ብዙ ላይጠይቅ ይችላል። ለሰርጎ ገብነት የሚታጨው ብቃቱ ከተጠና በኋላ ስለ ተልዕኮው ደግሞ በቂ መረጃ ይሰጠዋል። እንዴት መረጃ መሰብሰብ እንዳለበት፣ በመንግስት ወይም ድርጅት ውስጥ ከማን ተጠግቶ ታማኝ መስሎ መገኘት እንዳለበት ወዘተ..ይነገረዋል።ለምሳሌ ወያኔ ስልጣን ከያዘ በኋላ የሚመለምላቸውን ሰርጎ ገቦች ጭፍን "ፀረ ትግሬ" ሆናችሁ ቅረቡ እንደሚላቸው የታወቀ ጉዳይ

ነው:: ሰርጎ ገቦች የጀርባ ታሪካቸው ቢቻል የማይታወቅና ለጥርጣሬ የማይሰጥ መሆን ሲገባው ይህ ባልሆነበት ደግሞ በቂ ሽፋን በጥንቃቄ ይዘጋጃል:: በደርግ ጊዜ ሰርጎ ገብ ዕጩዎችን አስሮና ደብድቦ ተቃዋሚ ማስመሰል ወይም ከእስረኞች መሀል መወርወር የተለመደ ነበር:: ኢሕአፓ ሰርጎ ገቦቹን በቅድሚያ እያወገዘና እየኮነነ ለስራቸው ሲያመቻች በደህንነትና መካላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ያሰማራቸውን አባሎቹን የጠላቸው ለማስመሰል በጥይት ይስታቸው ነበር:: ዛሬ ወያኔ በየድርጅቱ የሰገሰገው የሰርጎ ገብ ቡድን አባላት በፀረ ወያኔነት ሳይወሰኑ በፀረ ትግሬነትም ያዙን ልቀቁኝ የሚሉ እንዲሆኑ መመሪያ የተሰጣቸው ናቸው:: በናይሮቢ ከተማ በወያኔ ሰላዮች በጥይት የተገደለው የቦረናው ተወላጅ መብዓ ፅዮን ወይም ጃተኔ አሊ ኃየሎም ሳዘዘው ግድያ የተመቻቸው ታማኙ በነበረውና በወያኔ በተመለመለው ጉዮ በተባለ የቦረና ተወላጅ አማካይነት ነበረ :: በደህንነት ተቋም ለምሳሌ ወያኔ የኢሕአፓ መምሪያ የሚባል ቀደም ብሎ የመሰረተ ሲሆን ዛሬ ደግሞ የኦነግም መምሪያ አለው:: አንድ ከወያኔ የከዳ የፀጥታ መኮንን እንደገለፀው ከሆነ ደግሞ በድርጅቶች ውስጥ የተላኩትን የከፍተኛ ደረጃ ሰርጎ ገቦች በተመለከተ ወያኔ ለሁሉም አሳውቆ የሚሰራው ባለመሆኑ በተወሰኑ የትግራይ ተወላጅ መኮንኖች ብቻ የሚታወቅ ነው:: ይህ ደግሞ በፀጥታ አሰራር አግባብ ያለው ነው:: ማንም ማወቅ ካለበት መረጃ ውጪ ማወቅ የለበትም:: መካለል የፀጥታ አሰራር አካል ነው::

ሰርጎ ገቡ የመጣባትን ያወግዛል ወይም ከዚያ ይርቃል:: የወያኔ ሰርጎ ገብ ስለ ወያኔ የተለሳላሰ ቅስቀሳ አያደርግም:: ይህ ማለት ግን ሁሉም ፅኑ ፀረ ወያኔ ሰርጎ ገብ ነው ማለት እንዳልሆነ ማወቅ ያሻል:: መንግስታት ድርጅቶችን በሰርጎ ገብ ሞልተናል ብለው ማስወራቱ ተቃዋሚዎች እርስ በርስ በጥርጣሬ እንዲተያዩና እንዲሸበሩ ስለሚያደርግ ይጠቀሙበታል:: የአሜሪካ የስላለ ድርጅት በተለይም ኢፒዲኤ ከተባለው ጋር በመተባበር የሀሰት ሰነዶችን በደርግ ላይ አሰራጭቷል--ደርግ የፃፈው በማስመሰል:: የመለስ መንግስት ዛሬ በድርጅቶች ማህተም ሰነድ ይረጫል:: ሰላዮቹን ጠላቱ ለማስመሰል ይኮንናቸዋል፤ አስሮም የፈታቸው እንዳሉ ያያነው ጉዳይ ነው::

5. <u>ለሰርጎ ገቦች አመቺ የሆኑ ክስተቶች</u> ዛሬ በርክተዋል፤በዝተዋል:: ህጋዊ መሆን ስለተባለ የድርጅትን ምስጢር በመሸፈን ረገድ ለቀቅተኝነት ሰፍኗል:: ጠላትን አለማወቅ ደግሞ ሁሉንም ገላጭ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም:: ዕድሜ ለኢንተርኔት ሁሉም ለሁሉም የሚቀርብ ሆኖ ይገኛል:: ይህ ለሰርጎ ገቦች ስራ በቂ ክፍተት ይፈጥራል፤ያመቻቻል:: ተቃዋሚዎችም እንደ ድሮው የጠላታቸውን የደህንነት መዋቅር የሚያጠና ክፍል የላቸውም:: ሰርጎ ገቦችን በወያኔ ላይ ቢያንስ በበቂ አላሰማሩም ማለት እንችላለን:: ድርጅቶች ለሰርጎ ገቦች ከሚያመቻቹ ሁኔታዎች አንዱ ክፍትና ልቅ ምልመላ መሆኑ ግልፅ ነው:: ሆ ያለን ሁሉ ደጋፊ ብሎ መመልመሉ ምንኛ ለወያኔ አመቺ እንደሚሆን በ "ያያ ጉለሌ" ቢሮአችን መጣ ያሉትን ሁሉ የመለመሉት ኦነጎች ለስዬ አብርሃ ሰርጎ ገቦች ክፍት ሆነው ለውድቀት መዳረጋቸው የሚታወስ ነው:: በተደጋጋሚ ኦነግ ጦር ለማሰማራት ያደረገው ሙከራ ለምን ከእንጭጩ ሲጨናገፍ ታየ? ወያኔ መረጃ ከየትና እንዴት አገኘ? ሁላችንም እንደምናውቀው የቅንጅት ስብስብ እንደ ሰነፍ በረት ክፍት ሆኖ መቆየቱ የታየ ጉዳይ ነው:: የአባላት ማንነትን ቀርቶ ለአመራር የበቁትንም ታሪክ ሆነ ጀርባ በተመለከተ የተደረገ በቂ ጥናት አልነበረም:: የብሄረሰብ ቡድኖች ደግሞ የብሄረሰባቸው አባል ሁሉ ታማኝ መሰ.ሎ ስለሚታያቸው ለሰርጎ ገቦች የተጋለጡ ናቸው:: የዚህ ጉድለት ወይም ድክመት መዘዙ ምን ለመሆኑ መዘርዘር አልገደድም:: ስለ ወያኔ የሰርጎ ገብ አሰራር ወይም ስሪትም በበቂ መረጃ ተቃዋሚዎች አልሰበሰቡም ብንልም ትክክል ነው::

6. <u>ሰርጎ ገቦችን እንዴት ለማሸተት ይቻላል</u> ስንልም አንዳንድ መለያዎችን መጠቆም ይቻላል::

- በየጊዜው አለምንም ልንረዳው በማንችለው መንገድ አቅዋም የሚቀያይሩና ክፍፍልን የሚያጅቡ
- ተቃዋሚ ድርጅቶች እንዳያብሩ ሸንጣቸውን ገትረው የሚታገሉ
- ባሉበት ድርጅትም ክፍፍልን የሚያራግቡ
- ፅንፍ አቅዋምን ገፍተው ክፍፍልን የሚደግፉ
- ስራቸው በጥንቃቄ ሲገመገም ክፍፍልን የሚያነግስ
- የጀርባ ታሪካቸው አጠራጣሪ ወይም ድብቅ የሆነ

***ይህ ሀሉ ግን በራሱና በነጠላ ሰርጎ ገብን ይገልጣል ማለት አይደለም፡፡ ጥናት ክትትል ይጠይቃል፡፡***

***7. <u>እውን ቅንጅት በሰርጎ ገቦች ተጠቅቷልን?</u> በበኩሌ ጥርጥር የለኝም፡፡ ሁለቱም አሁን በአሜሪካና አውሮጳ እየተናከሱ ያሉት ክፍሎች መሰረታዊ የፖለቲካ ልዩነት የላቸውም፡፡ ክፍፍሉ ማንን ጠቀመ ብንልም ቅንጅትና ሕዝብን ሳይሆን ወያኔን ነው፡፡ወያኔ ፈንድቋል፡፡ ልዩነቱና ችግሩ በውሰጥ በአግባብ ተይዞ መፍትሄ እንዳይገኝ በማጋለጥና በማራገብ እነማን ዘመቱ? እነዚህስ ትላንት የእነማን ደጋፊ ነበሩ? ይህ ሁሉ ሲጠየቅ ቅራኔው የተባባሰው በሰርጎ ገቦች አራጋቢነት ፖለቲካ ብሰለት በጎደላቸው ግን ቅን ልቦና ባላቸው የድርጅቱ ሰዎች መሆኑ ይታያል፡፡ የወያኔና ኢሕአፓን ውስጣዊ ክፍፍል ደርግ ተጠቅሞበታል፡፡ ጀብሃና ሻዕቢያንም በተመለከተ እንዲሁ፡፡ እነዚህ ግን በፖለቲካ ጥያቄ የተለያያአቅዋም የተከፋፈሉ ነበሩ፡፡ ቅንጅት ግን ተመሳሳይ አይደለም፡፡ ሁለቱም አንጃዎች ቢሆኑ ብዙ አባል ያልተቀበለውን ትብብር/ኤኤፍዲ ይደግፋሉ፡፡በቅንጅትም መርህ እናምንበታለን ባይ ናቸው፡፡ ታዲያ ግጭቱ የስልጣን ሹክቻ ነው? ይህ ከሆነ ደግሞ የታየና የሚጠበቅ ክስተት ነውና የመሪዎችን የስልጣን ሹክቻ ድርጅቱ ማስተናገድና በአግባብ መያዝ በቻለም ነበር፡፡ ይህን ልዩነት ማባባስ የሰርጎ ገቦች ስራ ነው፡፡ አንዱን ወገን ደግፈው ሌላውን ያወግዛሉ፡፡ከመቅፅበት አንዱ ዘራፊ ከሀዲ ሌላው ደግሞ የወያኔ ሎሌ ሆኖ ይፈረጅና ይወገዛል፡፡ መለሳለስ የለም፤ለመግባባት መጣር የለም፡፡ ፅንፈኝነትና ጥላቻ ይሰፍናል፡፡ ድርጅቱ ይከፋፈላል፤ ይዳከማል ብሎም ይከስማል፡፡ ዛሬ የሰርጎ ገቦችን ስራ ለምናውቀው ሁሉ ሕዝብ አመኔታ ጥሎበት የነበረው ቅንጅት ቢያንስ በውጭ ሀገር በወያኔ ሰርጎ ገቦች ለመቦርቦሩ ብዙ ምልዕክቶች አሉ፡፡***

***ለዚህም ነው ወገኔ ሆይ ጠንቀቅ በሉ ማለቱ ግዴታችን የሆነው፡፡ ተመክሮው ካለንና ካላቸው ለመማር መጣር አስፈላጊ ሲሆን የወያኔን መሰሪ ስራ የሚያውቁትም የቅንጅት ወገኖቻችንን ማስጠንቀቅ መምከር ግዴታቸው ይመስለኛል፡፡ በሶቭየት ህብረት ስንማር ብዙ ፀረ ሶቭየትና ቻይናን ደጋፊ ቡድኖች በሶቭየት ሰላዮችና ሰርጎ ገቦች የተያዙ እንደነበሩ ያወቅን ሲሆን ሶቭየት ህብረትም ሲፈረስ ይህ ሀቅ መሆኑ በሰነድ ተረጋግጧል፡፡ የባዕድ ኃይሎችም በዚህ መስክ እንዴት እንደሚሰሩ በቂ መረጃ አለ ፡፡ ይህን ሁሉ መመርመር ይገባል፡፡ ቅንጅት መከፋፈሉ ለማን ይጠቅማል? ይህን ክፍፍል ማን ያራግባል? ቅንጅትና ህብረት እንዳያብሩ ማን ይጥራል? መኢአድና ኢዴፓ አንዳይዋሀዱ ማን ጣረ ? በቅንጅት መሪዎች መሀል ክፍፍልን ማን አራገበ ? ዛሬ ፅንፌኛ ሆነው የሚታዩት ትላንት አቅዋማቸውሠምን ነበረ? የባዕድ ሎሌዎችሰ እነማን ናቸው? ይህን የመሰሉ ጥያቀዎች በመደርደርና ተገቢውን መልስ በመስጠት ወደ ሀቁ መጓዝ እንችላላን፡፡ የቅንጅት መጠናከር ለትግላችን አስፈላጊ ነውና ክፍፍልን የሚያራግቡ ሰርጎ ገቦችን ለማወቅና ለመመንጠር መጣር ደግሞ ግዳጃችን ይሆናል፡፡ ጠበቃ ነን ባዮቹ የወያኔ አቃቤ ህጎች እንዳይሆኑ ማለት ነው፡፡***

***ነቃ ብለን ድርጅቶቻችንን እንከላከል!***
***የተቃዋሚ ድርጅቶችን ህብረት እንደግፍ!***